ስማችን - ኢወክንድ
ልሳናችን - ነቅንቅ

## የአኟዋክ ወገኖቻችን ንፁህ ደም

## ዛሬም ትኩስ ነው !

## ልዩ መግለጫ

ታህሣሥ 2003

በምዕራቡ የኢትዮጵያ ግዛት ለሀገራቸው ቀናዒ የሆኑት የአኟዋክ ተወላጆች ፥ በዘመናዊዎቹ የትግራይ መሳፍ ንት የዘር ማጥፋት ፍጅት ከተካሄደባቸው እነሆ ሰባት ዓመት ሞላው::

ጊዜ ዘልዛላ ነው የሚባለውን አባባል ዕውነትነቱን ያረጋግጣል ። የወንድሞችና የእህቶቻችን ደም ሳናስከብር ሰባት ዓመት እንደ ዘበት ሊሞላው ነው ።

የወንድሞቻችንን ደም አፍስሰው የጠጡ ወያኔዎች ዛሬም ያለፍርድ ተንሰራፍተው ስናያቸው፥ በሀፍረት እንሸማቀቃለን። እነሆ ንጥር ኢትዮጵያውያን የጋምቤላ ልጆችን ዘር አጥፍቶ፥ ለም የሆነውን ምድር ለባዕድ የሸጠ ወያኔ ከነግም ሥርዓቱ እስከ ዛሬ መቆየቱን ስናይ ክፉኛ ይፈታተነናል ። ከሰባት ዓመት በፊት ያን ገራ ገር ምድር ሸጦ ከማሌሽያ ኩባንያ ቀብድ የበላው እናት- ሻጭ ወያኔ በቅድሚያ ምድሩ ላይ ያሉትን ባለቤቶ ች መጥረግ ነበረበትና አኟዋኮቹን ፈጃቸው ። ሴት፥ እናት እህቶችን በባለቤቶቻቸውና በወንድሞቻቸው ፊት በዚሁ የወያኔ ጉጅሌ ታጣቂዎች ተደፈሩ ። ተቀጠቀጡ ። ምንም መከላከያ የሌላቸውን ንፁህ ዜጎችን ዘራቸውን አጠፉ።

በእነ መለስ ዜናዊ መሐንዲስነት በነ ዶክተር ገብረአብ ባርናባስ ፈታውራሪነት የተካሄደውን የዘር ማጥፋት ወንጀል፥ የኢሕአፓ ወጣት ክንፍ ድርጅት <u>እንደዋዛ አይመለከተውም</u> ። ዛሬ፥ የሰባተኛ ሙት ዓመትን ስና ስታውስ፥ የሚወዷቸውን ልጆቻቸውን፥ የሚያፈቅሯቸውን ወላጆቻቸውን ፥ እንዲሁም ከውስጣቸው ጥል ቅ ሀዘን የተሰማቸውን ወገኖች በሙሉ መፅናናቱን ይስጣቸው ስንል ፥ ከዚህ ጋር ተዳምሮ ሌሎቹ ከፍተ ኛ የሆኑ በደሎችና ወንጀሎች በኢትዮጵያ ሕዝብ ላይ በማካሄድ ላይ የሚገኘውን ይህንን ዘር-አጥፊ ዘረኛ ፋሽስት ሥርዓት ከነግሳንግሱ ለመጥረግ ቁርጠኛነታችንን በመግለጽ ነው ።

አማራን ከነነፍሱ ጉድጓድ መክተት፥ ኦሮሞን በጅምላ መጨረስ፥ ኦጋዴንን መጨፍጨፍ፥ የአኟዋክን ዘር ማ ጥፋት፥ ኢትዮጵያ ሀገራችንን ጨርሶ ለማጥፋት ከአቀደው የወያኔ ዘረኛ ፖሊሲ ጋር የተየያዘ ነው ። ይህ ርምጃ የብሄር- ብሄረሰብ እኩልነት ሳይሆን ፥ ተራ የወያኔ የአባባል ቅርሻት ከመሆን አይዘልም ።

የዛሬ ሰባት ዓመት ከተፈጁት አራት መቶ አኟዋኮች ዛሬ በሕይወት ቢኖሩ ከግማሽ በላይ የሚሆኑት ወጣቶ ች ነበሩና ፥ ዛሬ ለሚደረገው የነፃነት ትግላችን ይቀላቀሉን እንደ ነበር ጥርጥር የለንም ። ይህንንም የመ ሥዋዕት ዝክር ስናስታውስ ፥ እንደ ዜጋ ብቻ ሳይሆን ፥ እንደ አቻ ጓደኞቻችንን ቁመን እንዘክራቸዋለን ፤ ይህንን መግለጫ የምናወጣውም ፥ ለአትርሱን ሳይሆን ፥ ለአንረሳቸውም ጥሪ ማስተጋቢያ ይሆናል ።

Tel 202-291-5832 P.O.Box 56068 Washington DC 20040 e-mail: joineprpyl@google.com
www.eprpy.com

ውድ ኢትዮጵያውን ጋምቤላዎች ሆይ !

የኢሕአፓ የምጥ ግልገሎች የሆን ወጣቶች ነንና፥ አፍላም ነንና፥ ለአኝዋክ ሕዝብ በደል፥ ለአኝዋክ ከመሬታቸው መፈናቀልና ድንግል መሬት መቀማት በተገኘው ጊዜና ቦታ በደማችን ልንታደግ ቃል እንገባለን ። በዚህ አጋጣሚ ፥ለአኝዋክ ወጣቶች ዜጎቻችን በየትኛውም አመች ጊዜና ቦታ ከኢሕአፓ ወጣት ክንፍ ድርጅት ጋር ለመቀላቀል ስትሹ፥ በራችንን ከፍተን፥ እጃችንን ዘርግተን እንቀበላችኋለን ። እናብራለንም ፥ እንደራጃለንም፥ እንታገላለንም፥ እናቸንፋለንም ። ይህ ነው ጥሪያችን !

የወያኔ ሃርነት ትግራይን እንደ መንግሥት ቆጥራችሁ የጋምቤላን መሬት የገዛችሁ፥ ህንድ ተባላችሁ ቻይና ፥ ዐረብ ተባላችሁ ሌላ ፥ ለቃችሁ ትወጡ ዘንድ የትህትና ጥያቄያችንንስናቀርብ ፥ ኋላ ለሚደርሰው ጥፋትና ጥቃት ፥ የጋምቤላ ሕዝብን እንዳትጠይቁ አደራ እንላለን ።

የወያኔ መውደቅና የውላችሁ መቀደድ በአንድ ላይ እንደሚከሰት ከወዲሁ ማሳሰቢያ እንሰጣለን ።

ለኢትዮጵያ ሕዝብ ነፃነት እኩልነት

ደማችንን አንሳሳለትም !

የአኝዋኮች ነፍስ ፍርድ ታገኛለች !

ደማቸውንና ደማቸው ደማችን ነውና እንበቀላለን !

ኢ.- ወክንድ

EPRPYL

Tel 202-291-5832 P.O.Box 56068 Washington DC 20040 e-mail: joineprpyl@google.com
www.eprpy.com